# በግ እንኳን መካች ነው!



በደግ በገርነት ዝናን ያተረፈው፣
ትልቁ መጣፍም ቅዱሱ የሚለው፣
ዘሩን በልቶ ሊፍጅ ቀበሮ ሲያጠቃው፣
አንድ ላይ ከትሞ በግ እንኳ መካች ነው፡፡

ጨፌ ሲጎዘጎዝ ቢላዋ ሲሞረድ፣
እግሩ ተጎትቶ ሲጋደም ለስለት፣
ፈርገጥ ፈርገጥ ብሎ ተነስቶ ከመሬት፣
የአራጅ ዓይን ይዝቃል ሸኮና አርጎ ስለት፡፡

በሩቁ ሲታየው ቀበሮ ሲመጣ፣
መሆኑን ያውቅና የበጎች ባላንጣ፣
አንድ ላይ ከትሞ ሳይፈጥር ቀዳዳ፣
ለትግል ይዘጋጃል ሳይከዳ እንደ ባንዳ፡፡

ወገኑ ሲታረድ ትርፍራፍ ዛቂው፣
የዘሩ ደም ሲፈስ የአራጅን ቂጥ ላሺው፣
ዲግሪና ቆብ ጫኙ አሳማ ብቻ ነው፡፡

የበጎች ሊቃውንት ተአሳማ እሚለየው፣
ተቅየው አባሮ አገር የሚያሳጣው፣
ነጣጥሎ እያረደ ዘሩን የሚያጠፋው፣
የቀበሮዎች ጅብ ተሩቁ ሲታየው፣
ታቅፎ ተደጋግፎ በአንድነት መካች ነው፡፡

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
መጀመርያ ታህሳስ ሁለት ሺ አስር ዓ.ም.
እንደገና ሚያዝያ ሁለት ሺ አስራ ሶስት ዓ.ም.